# የገንዘብ ሚኒስቴር

# MINISTRY OF FINANCE

## ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሚሆነውን የኤሌክትሪክ እና የውሀ ፍጆታ መጠን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1021/2016

**DIRECTIVE NO. 1021/2024**
**A DIRECTIVE TO PROVIDE ELECTRICITY AND WATER CONSUMPTION EXEMPT FROM VALUE ADDED TAX**

**<u>ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሚሆነውን የመኖሪያ ቤት የኤሌክትሪክ ኃይል እና የውሀ ፍጆታ መጠን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1021/2016</u>**

**<u>A DIRECTIVE TO PROVIDE THE AMOUNT OF ELECTRCITY AND WATER CONSUMPTION FOR DOMESTIC USE EXEMPT FROM VALUE ADDED TAX DIRECTIVE NO. 1021/2024</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ወርሃዊ የኤሌክሪክ ሃይል እና የውሃ አቅርቦት (የታሸገ ውሃን ሳይጨምር) ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ እንደሚሆን በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ የተደነገገ በመሆኑ፤

WHEREAS, the Value Added Tax Proclamation provides that the supply of electricity and water (with the exception of bottled water) in an amount to be determined by a directive to be issued by the Ministry of Finance shall be exempt from the Value Added Tax;

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 አባሪ ሁለት አንቀጽ 1 (ነ) ለገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል።

NOW THEREFORE, in accordance with Article 1(m) of Annex 2 of the Value Added Tax Proclamation No.1341/2024, the following Directive is issued.

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ መመሪያ "ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሚሆነውን የመኖሪያ ቤት የኤሌክትሪክ ኃይል እና የውሃ ፍጆታ መጠን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1021/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1. **<u>Short Title</u>**

This directive may be cited as "A Directive to determine the amount of electricity and water consumption for domestic use exempt from Value Added Tax No.**1021/2024**"

2. **<u>ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ ስለማድረግ</u>**

1) ከዚህ በታች የተመለከቱት ለመኖሪያ ቤት የሚውሉ የኤሌክትሪክ እና የውሃ አቅርቦቶች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ ተደርገዋል፦

   ሀ) የ200 ኪሎ ዋት ሰአት ወርሃዊ የኤሌክትሪክ ፍጆታ መጠን፤ እና

   ለ) የ15 ሜትር ኩብ ውሀ (ከታሸገ ውሃ በስተቀር) ወርሃዊ ፍጆታ መጠን፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም፣ የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት እና በማስተላለፍ ሥራ ላይ የተሰማሩ አቅራቢዎች በጅምላ በሚያቀርቡት የኤሌክትሪክ ኃይል ላይ በአዋጁ መሰረት ታክሱን የመሰብሰብ እና ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ የማድረግ ግዴታ አለባቸው።

2. **<u>Exemption from Value Added Tax</u>**

1) The following supplies of electricity and water for domestic use are exempt from Value Added Tax:

   a) Monthly electricity consumption up to 200 kWh; and

   b) Monthly water consumption up to 15 cubic meters (excluding bottled water).

2) Notwithstanding the provisions of sub-article 1 of this article, suppliers involved in the generation and transmission of electricity are obliged to collect Value Added Tax on wholesale electricity supplied and remit it to the tax authority, in accordance with the Proclamation.

### 3. የሚጸናበት ቀን

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገንዘብ ሚኒስቴር እና በፍትህ ሚኒስቴር ድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ፣ ነሓሴ 2016 ዓ.ም**

**አህመድ ሺዴ**

**የገንዘብ ሚኒስትር**

### 3) Effective Date

This Directive shall enter in to force on the date of its registration by Ministry of Justice and posted on the website of the Ministry of Justice and the Ministry of Finance.

**Done at Addis Ababa, August, 2024**

**Ahmed Shide**

**Minister of Finance**